# ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 2 ህዳር ፲ ቀን ፪ ሺህ ፲፩ ዓ.ም.

## <u>የዘር/ቋንቋ ክልል ሲሉን አንድ ሀገር! ስንል</u>

(ድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://www.youtube.com/watch?v=-iPg6ugTanE)

“***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***” በሀገራችን ኢትዮጵያ እየታየ ያለው የለውጥ ውጋጋን መሠረታዊ የሀገሪቷንና የሕዝቧን ጥያቄዎች ሊፈታ ይገባዋል። እንኳን ኢሕአዴግ/ህወሓትን ይዞ በአዝጋሚ ለውጥ ለመፍታት ይቅርና ኢሕአዲግ/ህወሓት ተወግዶ ሙሉ በሙሉ ሥልጣኑን ሌላ ኃይል ቢረከበው እንኳ ሀገራችን የተደቀነባትን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት ጊዜና ብልሃት ጠያቂ ነው። የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና አጋሮቻቸው ይዘው የተነሱት የለውጥ አቅጣጫ ተገቢውን መስመር እንዲይዝ ከሁላችንም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከሲቪክ ማህበራትና ከሌሎች ድጋፍና እገዛ እንደሚያስፈልጋቸው ብንረዳም የከበባቸውን የተዳፈነ እሳት መዘንጋት አይገባም። ይህ የተዳፈነ እሳት ቤንዚን ጠብ እንዳይልበት ጥንቃቄንና ብልህ አመራርን እንደሚጠይቅ እየጠቆምን ፖለቲካ ደግሞ የሥልጣን ጥያቄ መሆኑንም መዘንጋት አይገባም እንላለን።

በሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ኢሕአዴግን አመራር አድርጎ ህወሓት የዘራው የዘር ሕገ መንግሥት ውጤትና አስከፊው ገጽታ እየታየ ነው። ለዚህም ምክንያቱ 27 ዓመት የተዘረጋው ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለልና የዘረኝነት ውጤት በመሆኑ፤ ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ተወግዶ፣ ኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት ሊገነባና ሀገሪቷን ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና ሊያሸጋግራት የሚችል በሕዝብ የተመረጠ አገዛዝና የግለሰብ መብትን ቀዳሚ ያደረገ ገደብ አልባ የዴሞክራሲ መብት ተግባራዊ ሲሆን ነው እንላለን። በመሆኑም ከዘርና ቋንቋ ሌላ ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አከላለል ያስፈልጋታል የሚለውን አማራጫችንን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለክቡር ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እናቀርባለን።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት የመጡባትን ወራሪ ኃይሎች አሳፍራና የግዛት አንድነቷን አስከብራ የኖረች ጥንታዊት ሀገር ነች። በውስጣዊ የእርስ በርስ ሹክቻዎችና የሥልጣን ፍለጋ በተለያዩ ጊዜያት የልጆቿን ሕይወት ያለአግባብ ብትሰዋም የውጭ ወራሪ መጣ ሲባል ግን የሚጋደለው አንድ ይሆናል፣ መሣሪያ የተማዘዘው እጁን ከቃታው ያነሳል። የጥቁር ሕዝቦች፣ ለአፍሪካ ሀገሮች የነፃነት ጮራ የፈነጠቀው የ“ዐድዋ” ድል ለዚህ ምሳሌና አርአያ ነው። ሁሉም ተፋላሚ ጦሩን ጠላት ላይ ያነጣጠረበት፣ የተናቆረ ሁሉ እምቢኝ ለሀገሬ ብሎ የዘመተበት፣ ኋላ እንዳይጣላ ማንም ወስልቶ ያልቀረበት፣ ሴቶቻችን ጥልቅ ችሎታቸውን ያሳዩበት . . .ይህ ሁሉ ጉዞ ሀገር ሲባል የሙታን ዓጽም ይገላበጣልና ነው። “. . . ሀገር የሞተች እንደሁ በማን ይለቀሳል” ለተባለላት እናት ኢትዮጵያ ሙታን ዋጋ ከፍለዋልና።

ኢትዮጵያውያን ጥቃትን ባለመውደዳችን፣ በባዕዳን መረገጥን ባለመቀበላችን የሀገራችንን ክብር በመፈለጋችን ዐድዋን አስመዝግበናል። ቀደም ሲልም ዶጋሌን በአሉላ፣ መተማን በዓፄ ዮሐንስ፣ መቅደላን በዓፄ ቴዎድሮስ፤ ወራሪዎች ከሽንፈት ታሪካቸው አልተማሩም እንጂ አሳይተናቸዋል። ይህ አትንኩኝ ባይነት ታድያ እርስ በርሳችን ሲሆን ያሳዝናል። ነገሥታቱ በእግዚአብሔር ስም ገዝተዋል፣ እንዳይጠየቁ በእምነት አስረውናል። ደርግ በማርክሲዝም፣ ሌኒንዝም ካባ ከኔ በቀር አብዮተኛ ብሎ ትውልድ ፈጅቷል። ኢሕአዴግ/ህወሓት ቀዳሚው "ብሔር/ብሔረሰብ" ነው ብሎ የዘር ጥቃት አድርሷል፣ የሀገር ሉዓላዊነት እንዲደፈር እስከ መገንጠል በሕገ መንግሥት ደረጃ "መብት" ሰጥቷል።

ህወሓት/ወያኔ እስካመቸው ሀገሪቷን እየቦጠቦጠና ትውልዱን እያዳከመ ሊገዛ፤ ካቃተው የቀበረው የዘር ፈንጂ እንዲፈነዳ ዕቅዱ ነበርና ዛሬ እዚህ ደረጃ ላይ እንገኛለን። "ታላቋን ትግራይ ሪፓብሊክን" የመመሥረት የቅዠት ዕቅዱ ቅድመ ዝግጅት የትግራይ ግዛትን ከምዕራብ፣ ከምስራቅና ከደቡብ አጎራባቾች እየቀማ፣ እያስፋፋና ቀደምት ነዋሪዎችን እየበተነና እያጠፋ ዛሬ ላይ አድርሶናል። ወያኔ/ህወሓት በዘረጋው ዘርንና ቋንቋን ተገን ባደረገ ከፋፋይ አከላለል ዛሬ አንዱ ዘር ሌላውን እንዳይጠጋው፣ እንዲጠራጠር፣ መተማመን እንዲጠፋ አደረገበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በዘርና በቋንቋ የከፋፈላቸው ዘጠኙ የክልል "መንግሥታት" በውስጣቸው ያቀፏቸው ጎሳና ነገዶች የማንነት ጥያቄ በማንሳት በየአካባቢው የሚታየው ግጭት ሌላ ሳይሆን የኢሕአዴግ 27 ዓመት አገዛዝ ውጤት ነው። ሶማሌው ከኦሮሞ፣ ኦሮሞ ከአማራው፣ ደቡቡ ከኦሮሞ፣ ጋምቤላው ከአገዛዙ፣ ትግሬው ከሁሉም እየተናቆረና ደም እየተፋሰሰ ያለበት ወቅታዊ ሁኔታ፤ ዘረኝነትንና የቋንቋን አከላለል በአግባቡ ልንፈታና ከቶም እንዲያበቃ ማድረግ ካልቻልን ሀገራችን የምታሳየው ለውጥ እልቂትና መበታተን እንዳይሆን ያሰጋናል።

"***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ስማችንም እንደሚጠቁመው ኢትዮጵያ አንድ ሀገር መሆኗን፣ ሕዝቧም ሕዝቦች እንዳልሆኑ አጠንክሮ ይገልጻል። ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ሰንደቅ ዓላማችን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ብለን ስንነሳ ኢሕአዴግ አመጣሹን የሀገሪቷን በቋንቋና በዘር የመከፋፈል አባዜ እንዲያበቃ እየታገልን ነው።

እንደ ፖለቲካ ድርጅት የኢትዮጵያን የግዛት አከላለል በተመለከተ ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገው የግዛት አከላለል አደገኝነቱን 27 ዓመት ተመልክተነዋልና ሀገርንና ሕዝብን ከተደቀኑበት አደገኛ ጥፋት ለማዳን አማራጭ ያልናቸውን የሀገሪቷን አከላለሎች እናቀርባለን። ይህ አማራጭ በእኛ በኩል የቀረበና ሌሎች ቢጋሩትም ወይም ከሚያቀርቡት ጋር ተመክሮበት ያለምንም ማወላዳት ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ያበቃ ዘንድ የተዘጋጀ አማራጭ ነው።

በኢትዮጵያችን ያሉት የባሕል፣ የቋንቋ ዕኩልነት ወይም የልማት መስፋፋት ለሁሉም አለመስተካከልና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች፤ ችግሮች ቢኖሩምና በነዚህም ምክንያት የሚፈጠሩ ቅሬታዎች፣ የመብትና የተጠቃሚነት ጥያቄዎች፤ በአስተዳድር፣ በምርጫ፣ በሕግና ደንብ እንዲሁም ተጠያቂነትና ግልፅነት ያላቸውን ተቋማት በመመሥረትና በሂደት ይፈታሉ ብለን እናምናለን። ክልል አስምሮ ዘሬ፣ ነገዴ፣ ጎሣዬ ተበድሏል ስለዚህም "ካኮረፍኩ ክልሌን ይዤ እገነጠላለሁ" እየተባለ የተፈለገው ልማትና ዕድገት ቀርቶ ባለፈው 27 ዓመታት ከታየውና በጎረቤት ሶማልያ፣ ደቡብ ሱዳን ከደረሰው የባሰ ግጭትና ብጥብጥ ወደ ሀገርን የማጥፋት ደረጃ ሊሸጋገር ይችላል። ጥቂት ልሂቃን ብዙውን ሕዝብ እንወክልሃለን፣ እናውቅልሃለን ከማለት አልፈው የኢትዮጵያችንን ክፍሎች እንደ መያዣና ማስፈራሪያ የሚያደርጉበት የመንግሥት አወቃቀር መቀየር አለበት። የ27 ዓመት ተመክሮ የሚያሳየው ይህንን ነው።

እንኳን እንደ ኢትዮጵያችን ያሉ ከትውልድ ትውልድ የሚተርፍ ብዙ በዕድገትና ዘመናዊ ሥልጣኔ ሥራ የሚጠብቃት ሀገር ቀርቶ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ብዙ የቀደሙን ሀገራትም የመንግሥት መዋቅርን የሚዘረጉት ሀገሮቻቸውን የሚከፋፍሉት በቅድሚያ ለአስተዳደር፣ ለምጣኔ ሀብት እድገት፣ ለፀጥታ፣ ለሰላምና ለመሳሰሉት ጉዳዮች አመቺ እንዲሆን ብቻ ነው።

በ “*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ*” አመለካከት ቀጣዩ የሀገራችን የግዛት አከላለል አስመልክቶ ሦስት አማራጮች እናቀርባለን።

1. የቀድሞው ክፍለ ሀገራዊ አስተዳደር (ሥዕል 1)




ይህኛው አከላለል ኢትዮጵያን ከኤርትራ በቀር በ13 ክፍለ ሀገራት አስተዳደሮች ያካልላታል። በዚህ አከላለል አሁን ከአለው የዘር አከላለል ቢሻልም የተወሰኑ ዘሮችን በአንድ የዘር ክልል ወይም የማንነት ዝንባሌ ውስጥ ያስቀምጣል። ለምሳሌ ትግራይ ክፍለ ሀገር አሁንም የዘርና የቋንቋ አከላለልን መያዙን ያመለክታል። ጎንደር፣ ጎጃም ወሎ የመሳሰሉትም በአማራ ነገድ ወስጥ የእኔነት ስሜትን መፍጠራቸው አይቀሬ ነው። እንዲሁም ወለጋ፣ አሩሲ መሰል ክፍለ ሀገራትም እኛነን ኦሮሞ የሚል የማንነት ስሜትን እንደሚያጎላ ይገመታል። በተለይ የኢሕአዴግን የዘርና ቋንቋ አከላለል የጣለውን የዘረኝነት ስነልቦናዊ ጥቃት እንደያዙ ወደዚህ ክፍለ ሀገራዊ አስተዳደር መሸጋገሩ ችግሩን በመጠኑ ከማቃለል ሌላ ሙሉ በሙሉ መፍትሄ ያስገኛል ወይ? የሚለውን በጥያቄ ያስቀምጠዋል።

2. የአውራጃ አከላለል (ሥዕል 2)




ኢትዮጵያን በአፄው አስተደደር ዘመን የወጣውን የአውራጃዎች አከላለል መሠረት በማድረግና የሚሻሻልም ካለ አስተካክሎ በአውራጃ ደረጃ ማካለሉ ያለውን ዘረኝነት በሂደት ይበልጥ ይሰብረዋል የሚል ግምት ሌላው አማራጭ ነው። በዚህ ጥናት መሥረት በኢትዮጵያ ከ90 የማያንሱ አውራጃዎች ሲኖሩ እያንዳንዱ አውራጃ የየራሱ አስተዳደራዊ ክልል ይኖረዋል። ይህ አከላለል በሀገሪቱ የሚያስፈልገውን ዋነኛ የግለሰብና የዜግነት መብት ቅድሚያ ትኩረት እስከተሰጠው ድረስ እያንዳንዱ የአውራጃ ክልል ትኩረቱን ወደ ልማት በማዞር በሚመደብለት ዓመታዊ በጀት አንዱ አውራጃ ከአንዱ የልማትና የእድገት ፉክክር ውስጥ እንዲገባ ይጋብዘዋል። በተጨማሪም በዘር የተካለሉ አካባቢዎችን ሳይቀር ወደ አውራጃ በመከለል የራሳቸው አስተዳደራዊ ክልል ስለሚኖራቸው የጎላውን የዘረኝነት አክሄድ ይቀርፈዋል ብለን እናምናለን።

3. *መልክዓ ምድር (ጂኦግራፊያዊ) የተፋሰስ ወንዞች አከላለል (ሥዕል 3)*




*ጂኦግራፊያዊ የኢትዮጵያ ወንዞችንና ተፋሰሶችን አከላለል አማክሎ ሲካለል የየክልሉም አጠራር በተፋሰሱ ወንዞች ይሆናል። ይህ ያለውን የሀገሪቷን አከላለል ብዛት ሲያሳንሰው በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ጎሳዎች/ነገዶችን አብሮ የመኖር ትስስርን ይበልጥ ያጠነክረዋል። ይህ አከላለል በግለሰብ ደረጃ እንኳ ጎሳዬ/ነገዴ ከዚህ ነው ያስብላል እንጂ ክልሌ ይህ ነው የሚለውን በማስወገድ ጥሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የተፋሰሶች አከላለልና ስያሜ በሥዕሉ (3) እንደተመለከተው አዲስ አበባን ሳያካትት ብዛታቸው 10 ሲሆን ስያሜአቸውም ተከዜ ተፋሰስ፣ አፋር ተፋሰስ፣ ዐባይ ተፋሰስ፣ አዋሽ ተፋሰስ፣ ባሮ አኮቦ ተፋሰስ፣ ኦሞ ተፋሰስ፣ ስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ፣ ገናሌ ዳዋ ተፋሰስ፣ ዋቢ ሸበሌ ተፋሰስ እና ኦጋዴን ተፋሰስ ይሆናል። ተፋሰስ የሚለውን ሁሉም የኢትዮጵያ አካል ስለሆኑና ይህን ይበልጥ ለማጠናከር ክፍለ ሀገር በሚለው መተካት ይቻላል። ይህ አከላለል ሌላው ጠቀሜታው ሁሉንም ዘር ትግሬውን ከሌላው፣ አማራውን ከሌላው፣ ኦሮሞውን ከሌላው፣ ሌላውንም ከሌላው ቀይጦ ስለሚያካልል በሂደት ለሀገራችን ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን ይበልጥ እንድናዳብር ይጠቅማል። ይህ ሲሆን ባህላችንን፣ ቋንቋችን፣ ሃይማኖታችንና በሂደትም ዘራችንንም አብሮ በመኖር፣ በመጋባት እየተጋራን ያሉንን ቋንቋዎችና የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች እንዳይረሱ ደግሞ ሁሉም ኃላፊነት ወስዶ እንዲያዳብረው፣ እንዲንከባከበው ይረዳል።*

*ከላይ ያቀረብናቸው ሦስት አማራጮች ሌሎች ሊያቀርቧቸው ከሚችሉት ጋር ተዛምዶና ለውይይት ቀርቦ ኢትዮጵያ ሀገራችንን እንደ ሀገር ማስቀጠልና የሁሉም ነገድ/ጎሳዎች ክልል ኢትዮጵያ እንድትሆን እስከተስማማን ድረስ ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ማብቃት ይኖርበታል ባይ ነን።*

*ኢትዮጵያ የመልካም አስተዳደርና የዜግነትና የግለሰብ መብትን ቅድሚያ ሰጥታ በዴሞክራሲያዊ ጎዳና እስከተራመደች ድረስ በዚህ አከላለል መሠረት የጎሳ ፋክክር ቦታውን ለልማትና ዕድገት ፋክክር ይለቃል የሚል ጽኑ ዕምነት አለን። ሊሠመርበት የሚገባው ዋና ቁም ነገር **<u>የዘርና የቋንቋን አከላለል ማስውገዱ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ያልተገደበ የሰው ልጅና የግለሰብ መብት የተከበረባት ሀገር መሆኗ ነው።</u>***

*በተጨማሪም በኢሕአዴግ መንግሥት እንዲፈርስ የተደረገው የቀድሞው የብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ከረጅም ዓመታት ጥናት በኋላ የቀረቡ የኢትዮጵያን መንግሥት አስተዳደር በሚያመች መልኩ የሚያዋቅሩ አማራጮችም እንደ ተጨማሪ ሃሳብ መታየታቸው በጣም ጠቃሚ ነው።*

*አሁን ያለው የጠቅላይ ሚኒስትር ዶር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት በዚህ 27 ዓመት ለዘለቀው ሕገ መንግሥትና "በምርጫ" ለተቋቋመው ፓርላማና ሌሎች ሕግጋት ተገዢ ቢሆንም፡ ይህ ጉዳይ ግን ኢትዮጵያችን ላይ ከተጋረጠው የዘር ፖለቲካ ግጭትና መፈናቀል አሳሳቢነት ምክንያት ውይይቱና አማራጭነቱ ከአሁኑ ጊዜ ጀምሮ ለሕዝብ መቅረብ ይኖርባታል።*

ሀገርን በዘርና በቋንቋ በመከለል አይደለም ቋንቋም የሚዳብረው፣ ሀገርም የሚለማው። በኢትዮጵያችን ያሉ በርካታ ጎሳ/ነገዶችንና የተለያዩ ቋንቋዎቻችንን ልናዳብርና በታሪክ ቅርስነት ልንጠብቃቸው የምንችለው አጥር በማጠር ሳይሆን በተቋማት ደረጃ ጥናትና ምርምር እየተደረገ ሲጠበቁ ነው። ለዚህ ደግሞ ኃላፊነቱ የአንዱ ጎሳ/ነገድ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ነች።

<u>አንድ ሀገር ስንል</u>

ኢትዮጵያ በመላው ዓለም እንደ አንድ ሀገር ታውቃ ነው የቆየችው። በጥንት ዘመናት የአገሪቱ የመሬት ስፋትና የሕዝቧ ስብጥር እንደ ሌሎች የዓለም አገራት ሲቀያየር ነበር። ኢትዮጵያ በምትገኝበት ቀጠና ምክንያት ለዘመናት ሙሉ ሀገሪቱን ወይም ከፊል መሬቷን ለመቀማት፣ ሕዝቧን በቅኝ ለመግዛት፣ ሃይማኖት ለማስፋፋት ወይም ለማስቀየር እና በሌሎችም በዓለማችን ታሪክ በየጊዜው በተነሱ ምክንያቶች በኃይል የመያዝና የማንበርከክ ብዙ ጦርነቶች ተከፍተውባታል። ይህንን ሁሉ እንደ አመጣጡ ተቋቁማ እስካሁኑ ድረስ ***"አንድ ሀገር"*** ሆና ዘልቃለች። በአፍሪካ ቀርቶ በሌላው ዓለምም ይህን ያህል ዘመናትን ያስቆጠረ የ***"አንድ ሀገር"*** መሠረት ያላቸው ሀገራት ብዙ አይደሉም። ይህ ለዘመናት ባስቆጠረ መሠረት ላይ የፀና ***"አንድ ሀገር"*** መሆን በታሪክ ሂደት ካልሆነ በአጭር ጊዜና በመሪዎች አዋጅ ወይም በግዴታ ውል የማይገኝ ትልቅ በሔራዊ እሴት ነው። ይህ እሴት መዳበር መጠናከርና ለሁሉም ሕዝብ ዋስትና እንዲሆን በሕገ መንግሥት መጠበቅ ያለበት የኢትዮጵያ ታሪክ ዋና መሠረት ነው። በቀላሉ የተገኘ ሳይሆን ብዙ ልፋትና መስዋዕትነት የተከፈለበት በመሆኑም የኢትዮጵያ ***"አንድ ሀገር"***ነት ለድርድር የሚቀርብ ሳይሆን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የህልውናው ዋስትና መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

የቅርብ ታሪክ እንኳን የሚያስታውሰን ኢትዮጵያ ከሊግ ኦፍ ኔሽንስ ጀምሮ እንደ ተባበሩት መንግሥታት (ዩናይትድ ኔሽንስ) ባሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የዓለም ሰብአዊ መብት ተቋም፣ የገንዘብ፣ የኢኮኖሚ፣ የሃይማኖትና ተመሳሳይ ድርጅቶች፣ በአህጉራዊና አካባቢያዊ ስብስቦች ሁሉ የምታወቀውም አባልነቷም እንደ ***"አንድ ሀገር"*** ነው። በዓለም አቀፍ ውሎች፣ በሰላም ማስከበር፣ በሽምግልና፣ በእስፖርትና በሌሎችም በተለያዩ የዓለም መድረኮች ዕውቅናዋና ተሳትፎዋ እንደ ***"አንድ ሀገር"*** - ኢትዮጵያ ነው። ሌላው ቀርቶ በየዘመናቱ ሊያጠቋት የተነሱ ጠላቶቿ እንኳን ኢትዮጵያን ከጥንት ጀምሮ እንደ ***"አንድ ሀገር"*** ነው የተመለከቷት የሚመለከቷትም። ይህ ሁሉ መጠበቅ ያለበት ብሔራዊ ሃብት ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ወደ ሥልጣኔ ተሸጋግራ የሕዝቧም ኑሮ አሁን ከሚገኝበት እጅግ የተሻለ ደረጃ ላይ እንዳይደርስ አንቀው የያዙት ችግሮች በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች የሚታዩ ናቸው። ለአብነት ያህል የኃይል ወይም ኤነርጂ አቅርቦት፣ የጤና አገልግሎትና የንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ የትምህርትና መገናኛ አገልግሎት፣ ዘመናዊና በዝናብ የማይስተጓጎል አስተራረስ (ከእጅ ወደ አፍ እርሻ ለመላቀቅ)፣ ወዘተ. የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ ችግሮች ሁሉም ክልል ዘርና ነገድ ዕኩል የሚጋራቸው በጣም መሠረታዊ ችግሮች ሆነው ሳለ ለአለፉት 27 ዓመታት ግን ትኩረት የተደረገው ለፖለቲካ ፍጆታ፣ ለሥልጣንና ጥቅም ሲባል ኢትዮጵያችንን በዘርና በነገድ ማካለል ነው። ቋንቋና ዘርን ተገን ያደረገ የክልል ፖለቲካ ለነዚህ መሠራታዊ ችግሮች መፍትሔ አለመሆኑ ከበቂ ጊዜ በላይ ታይቷል።

ለሁሉም ቁልፍ ደግሞ ተጠያቂነትና ግልፅነት ያለው ሕዝባዊ መንግሥት ነው። እነዚህና ሌሎችም እጅግ መሠረታዊ ችግሮች እየጨመረ ካለው የሕዝብ ቁጥር ጋር ተዳምረው ፋታ የማይሰጡና አስችኳይ መፍትሔ የሚፈልጉ ጉዳዮች ናቸው። በመላው ኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በጠቅላላው በሀገሪቱ ያሉ አሳሳቢ ችግሮች ናቸው። ይህ ዕውነታ የሚያስገነዝበን ችግሮቻችን ሳይቀር '*አንድ* ናቸው። እነዚህን እንደ *"አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ"* ተባብረን ለመፍትሔያቸው መረባረብን ይጠይቃል። መለያየቱ የድንበር፣ የፖለቲካ፣ የዝውውር ወዘተ ራስምታት ከመጨመር በቀር የሚፈይደው ወይም ችግሩን የሚያቃልለው አይደለም። በተለይ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት አንፃር - ከዚህ በፊት በሀገራችን ላይ የተደረጉ በደሎች (የሁለተኛውን የጣሊያን ወረራ ጊዜ ያስታውሷል) *"አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ"* ሆነንም ለመፍታት አስቸጋሪ ነው እንኳን ተከፋፍለን፤ የሀገሪቱን አንድነት በተመለከተም ልምምጥም፣ የሃሠት ታሪክ መፃፍም አዋጭ አይደለም።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት የተቆጠረ ታሪክ ያላት አገር ነች። ይህንን የውስጥም ሆነ የውጪ ጠላቶቿ የማይክዱት ሀቅ ነው። የኢትዮጵያን አመሠራረት፣ በተለያዩ ጊዜያት የነበረውን የግዛቷን ስፋትና ጥበት፣ የመሪዎቿን ዘርና ትውልድ እና ሌሎች ጉዳዮችን እያነሱ ቢሟገቱም ኢትዮጵያ የምትባል ጥንታዊ ሀገር እስከ አለንበት የአሁኑ ጊዜ መኖሯን መካድ አይቻልም። በዚህ ላይ የሚደረጉ የታሪክና አርኪዎሎጂ ውይይትና ጥናቶችን ለባለሙያዎች ትቶ በዚህ በኢትዮጵያችን ህልውናና ዕውነታ ላይ ተመስርቶ የሚከተሉት ሃቆች መረዳት አስፋላጊ ይሆናል - በተለይ አሁን ሀገሪቱ ባላችበት ሁኔታ ላይ ከረዥም ዘመናት ሀገር የመመሥርት የታሪክ ሂደት የተመሠረተች ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አለች። ኢትዮጵያችን በቅኝ ገዥዎች የተፈጠረች አይደለችም።

ኢትዮጵያችን ከላይ እንደተጠቀሰው የግዛት ድምበሯና የአስተዳደር ማዕከሏ ቢቀያየርም ከጥንት ጀምሮ አሁን በምትገኝበት መልክዓ ምድር አቀማመጥ ድንበሯን ጠብቃ በነፃነት ያለች አገር ናት። ይህ እንደሌሎች አገራት ሁሉ የተካሄደ ታሪካዊ ሀገር ምሥረታ ኢትዮጵያዊነት የሚል ስብህናና ማንነትን ፈጥሯል።

የዘመናዊ የመንግሥት አስተዳድር መመሥረት፣ በፍጥነት ማደግና መስፋፋት ለኢትዮጵያዊነት መስፋፋት ጥልቀትና መጠንክር አጋዥ ኃይል ሆኗል። የመንግሥት አስትዳደር መዋቅር በወረዳዎች፣ አውራጃዎችና ክፍላተ ሀገራት መስፋፋትና በውስጡ በያዛቸው ሠራተኞች ቁጥርና የዘር ቅልቅል በብዛት በነዚህ አካባቢዎች መሠማራት ኢትጵያዊ ማንነት የጋራ የዜግነት መገለጫ መሆኑን አጠናከረውም፤ አፋጠነውም። የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የዘር ስብጥርና የተሰማራበት አካባቢዎች፣ የትምህርት ቤቶች መስፋፋትና እንደ መከላከያው አባላት ሁሉ ከተለያዩ አካባቢና ጎሣ የተገኙ አስተማሪዎች መበተን፣ እንደነዚሁ ሁሉ የፖሊስ ሠራዊት፣ የጤና ጥበቃና ሌሎችም የመንግሥት ስራተኞች በነዚህ መዋቅራት መሠማራትና በዛው አካባቢ ኑሮን መመሥረትና የተከተለው ማህበራዊ ግንኙነት የጋራ ኢትዮጵያዊ ማንነትን አዳበረው መገለጫም አደረገው። ከዚህም ጋር ተያይዞ የከተሞች መቆርቆር ማደግና መስፋፋት ለሎች የግልና የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ማለትም እንደ ሆቴል፣ ትራንስፖርት፣ የኤሌክትሪክና የስልክ ወዘተ አቅራቦት ሰጪ ሠራተኞችም በየአካባቢው መሰማራት የቅልቅሉን ሂደትና የጋራ ኢትዮጵያዊነቱን አፋጠነው። ከዚህም በተጨማሪ ከምዕራብ አገሮች ባይወዳደርም ዘመናዊ ፋብሪካዎች፣ ኃይል ማመንጫዎች፣ የመገናኛና ትራንስፖርት ኢንዱስትሪዎች መሰፋፋት የከተሞችን ማደግና የኗሪያቸውን ቁጥርና ስብጥር አሳደገው። ከዚህም ተከትሎ በትንንሽም ከተማዎችም ሳይቅሩ በማህበራዊና ባህላዊ ግንኙነቶች ማለትም አብሮ በመሥራት፣ በጉርብትና፣ በዕድር ወዘተና በባህላዊው ግንኙነቶች በሠርግ ጋብቻና አምቻ፣ በአበልጅ ወዘተ እየታገዘ አንድ ኢትዮጵያዊ ማንነት ከጎሣና ዘር በላይ እየነጠረ ይወጣ ጀመር። ይህም በሌሎች ሀገሮች ከተደረገ የዜግነትና የማንነት አመሠራርት ሂደት ጋር ተመሳሳይ

ሲሆን ከጥንት የነበረውን የኢትዮጵያዊ ማንነት እርሾ በዚህ መልኩ በዘመናችን የኢትዮጵያዊነት ዜግነት መገለጫ ሆኖ ቀጥሏል።

የኢትዮጵያዊነትን ስሜት በማስፋፋት የክርስትና (ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት ወዘተ) እና የእስልምናና የባሕላዊ ዕምነቶች ተከታዮችና ተቋማት የራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል። በኢትዮጵያ ተቋቁመው የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ ኢሕአፓ፣ መኢሶን ወዘተ ኢትዮጵያችንን እንደ አንድ ሀገር የተቀበሉና ለኢትይዮጵያዊነት ስሜት መዳበርና ከእራስ ከተማና አካባቢ የሰፋ ሀገር አቀፍ አመለካከት እንዲዳብርና በኢትዮጵያዊነት ስሜት ሀገራዊ ችግሮችን ማንሳት፣ መጠየቅና ለመፍሔያቸውም መታገልን አስለምደዋል። የ"ብሔር ጥያቄ" በሚባለው ላይ የነበራቸው የየራሳቸው የአመለካከትና ያቀረቧቸው መፍትሔዎችም ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው።

በጥቅሉ ኢትዮጵያዊነት ከዘር ጎሳና አካባቢ፡ ከርዕዮተ ዓለም ወይም ከሌሎች የፖለቲካ አመለካከቶች በላይ የሆነ ከሁሉ የቀደመ የማንነት መገለጫ ነው። ያለግዴታ ፈልገው የሚቀበሉት ከዚህም በላይ ተያያዥ ለሚሆነው የዜግነት ግዴታ ተገዢ የሚሆኑበትና የሚመኩበት ማንነት ነው፤ ኢትዮጵያዊነት። በአጭሩ በምንም አይነት ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ፤ የሚጋደሉለትና የሚሞቱለት ማንነት ነው። ኢትዮጵያዊ ማንነት።

የዘረኝነትን ትርጉም ሁሉም ይረዳዋል ነገር ግን በተለይ በኢትዮጵያችን ሁኔታ አደጋው እየከፋ በመሄድ ከዕለታዊ ግጭት አልፎ በርካታ ሀገር አፍራሽ ሴራዎችና ተግባራትን በመቀስቀስ ይህን በታሪክ ሂደት የተመሠረተን ኢትዮጵያዊነትና የሀገሪቱን አንድነትና ሕልውና አሳሳቢ ደረጃ አድርሷቸዋል። የኢሕአዴግ አገዛዝና የዘር ፖለቲካ ድርጅቶች ሥራዬ ብለው የተያያዙት ይህነኑ አደጋ ማባባስና ሀገሪቱን መከፋፈልና መበታተን ነው፤ ለአለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት። ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለበት የኋላ ቀርነት የጋራ ችግርና ከዚህም ተከትሎ ለመጣው ድህነት የጋራ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ በዘርና በቋንቋ መከፋፈል ሀገሪቱንና ሕዝቧን የባሰ አዘቅት ውስጥ እየከተተ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በዘርና አካባቢ አድልዎ የሚደረጉ የልማትና ዕድገት እንቅስቃሴዎች የዜግነትና የማንነት ጥያቄዎችን በአፍራሽ መልክ እንዲነሱ አድርገዋል።

ለዚህ መፍትሔ የሚሆነውና ሀገራችን አሁን ከአለችበት ሁኔታ ወደ ሰላምና አንደነት የሚወስደው መንገድ ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!"*** ብሎ መነሳት ብቻ ይሆናል። ካለፈው ሃያ ሰባት ዓመታት የዘረኝነት አገዛዝ ተመክሮ ቀስመን ኢትዮጵያችንን ለትውልድ በማብቃት በታሪካችን ጥቁር ነጥብ ጥለን ላለማለፍ ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!"*** እንላለን።

***<u>የዘርና ቋንቋ አከላለል ማብቃት አለበት ስንል፡</u>***

ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት አብቦና ጎልብቶ ለሁሉም ልጆቿ ያልተገደበ የዴሞክራሲ መብት ያጎናፀፈች ሀገር እንገንባ ካልን ዘርንና ቋንቋን ያማከለ አከላለል ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እናዳመዘነ በአሳለፍነው 27 የኢሕአዴግ አገዛዝ ተገንዝበናል። የዘር አከላለልን ካስወገድንና የግለሰብ መብትን ተግባራዊ ካደረግን በኢትዮጵያ የትኛውም ግዛት ተኖሮ "ዘሬ ይህነው፣ ክልሌ ኢትዮጵያ" ባይ ትውልድ እንፈጥራለን።

ዘርንና/ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል በኢሕአዴግ አገዛዝ ዘመን ያስከተለውንና የሚያስከትለውን ውጥንቅጥ በመጠኑ እንቃኛለን፦

ሀ. በጎሳ/ነገዶች ውስጥ ያሉ ሌሎች ጎሳ/ነገዶች የማንነት ጥያቄ

ኢትዮጵያ ሀገራችን የበርካታ ጎሳዎች/ነገዶች ሀገር ናት። በእያንዳንዱ ነገድና ጎሳ ውስጥ ሌሎች በርካታ አሉ። ዋና ዋና የተባሉት ጎሳ/ነገዶች ማለትም አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ደቡብ ሕዝብ፣ ውስጥ ላሉት ሌሎች ጎሳዎች መብት ተሚጋች ማን ሊሆን ነው? አማራው፣ ኦሮሞው፣ ትግሬው ወዘተ ለብቻው ሲካለል በቀጣይነት በውስጡ ያሉ ሌሎችም ተመሳሳይ የማንነት ጥያቄ ማንሳታቸው የማይቀር ነው። ለዚህም ነው በቅርቡ የቅማንት፣ የራያ፣ የወልቃይት የማንነት ጥያቄ እየተባለ የተፈጠረው ችግር ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገው የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ውጤት ነው የምንለው።

ለ. የሌሎች ዘሮች መፈናቀል ጉዳይ

እያንዳንዱ ክልል በዘርና በቋንቋ መዋቀር ያስከተለው ውጤት ቢኖር ከክልላችን ውጡልን ሲሆን ይህ ደግሞ በተለያዩ ክልሎች ግጭት ብቻ ሳይሆን የበርካታዎችን መፈናቀል አስከትሏል፣ ሕይወት ቀጥፏል። በቅርቡ የተከሰተው በሶማሌ ክልል የኦሮሞዎች መጨፍጨፍና መፈናቀል፣ በደቡብ እንዲሁ፣ በወልቃይት የአማራዎች ስቃይ ሌላም ሌላ የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት የዘራው መርዘኛ የዘርና ቋንቋ አከላለል ውጤት ነው። ይህ ዜጎችን የማፈናቀል ጉዳይ ሊያበቃ የሚችልበት ዋነኛው ጉዳይ ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ሲያበቃ መሆኑ ሊጤን ይገባዋል። ይህ ካልሆነ በአንዱ ዘር ክልል ያለ ሌላ ዘር የልማቱም ሆነ የማንኛውም ጉዳይ ተጠቃሚ አይደለምና ግጭቱ እየተባባሰ ሀገሪቷን ወደማትወጣበት ችግር ውስጥ እንዳትዘፈቅ ቀድመን እናሳስባለን።

ሐ. ዘራቸው ኢትዮጵያዊ የሆነ

ይህ በተለይ እንደ አዲስ አበባ ዓይነት ከተሞችን ይመለከታል። አዲስ አበባ የሁሉንም ዘሮችና ቋንቋ ተናጋሪዎችን አካታ ያለች “*ትንሿ ኢትዮጵያ* ነች ቢባል ያስኬዳል። ሁሉም የመጣበት ጎሳ/ነገድ የሚናገረው ቋንቋ ሳያግደው የሀገሪቷን ቋንቋ አማርኛ በጋራ የሚግባባበት፣ አንዱ በአንዱ በዓል ላይ በደስታ እኩል የሚጨፍርበት፣ በሐዘኑ የዛሬን አያርገውና በአንድ አካባቢ እኩል ዕድር የሚጋራበት፣ በሃይማኖቱ መስጊድና ራጉኤልን በአንድ አጥር ያገናኘች፣ እስላሙ “ስለ እግዚአብሔር” ለሚለው የሚቸርበት፣ ክርስቲያኑ ለእስላሙ የሚረዳበት፣ በትምህርቱ ዘር ሳይታይ እኩል የሚስተናገዱባት፣ መሥሪያ ቤቶች ሁሉንም ዘሮች ያካተቱ፣ ኢትዮጵያዊነትን ነፀብራቅ የያዘች ናት፤ አዲስ አበባ። በመብትና በችግሩ ዘርና ቋንቋ ሳይለይ እኩል የተደበደበ፣ የታሰረ፣ የተሰደደ፣ የተገደለ ያስተናገደች፣ በረሃቡ እኩል የተገረፈ፣ በሥራፈትነቱ ሁሉም ዘር ለጎዳና ተዳዳሪነትና ሴቶቻችን ለሴተኛ አዳሪነት የተዳረጉበት ዘርፈ ብዙ ኅብረተሰብን ታቅፋ ያለች ናት፤ አዲስ አበባ።

አዲስ አበባ ይህንን ሁላ ይዛ የጎረምሳ ድብድብ ቢኖር በዘር ሳይሆን በአካባቢ (ካዛንችስ ከዑራኤል፣ ንፋስ ስልክ ከጎተራ፣ አራት ኪሎ ከፒያሳ ወዘተ) እየተባደነ ጊዜያዊ መቧቀስ አድርጓል እንጂ የዘር ግጭት ከቶም የሌለባት ነች። የአዲስ አበባ ልጅ በውስጡ የያዘውን ዘር ሳይለይ የመርካቶ ሠፈር፣ የፒያሳ አራዳ፣ የአራት ኪሎ ልጅ፣ ቀበና ሠፈር፣ የነፋስ ስልክ ልጅ፣ የካዛንችስ ጮሌ፣ የዑራኤል ልጅ፣ የቦሌ ጆሊ፣ ገርጂ፣ ላፍቶ፣ አየር ጤና . . . እያለ አካባቢያዊ አጠራር አለው እንጂ በመጠኑም ቢሆን ዘሩን መጥራት የተገደደው በኢሕአዴግ ዘመን ነው። ያም ሆኖ ዛሬም የአዲስ አበባ ነዋሪ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊነቱን እንጂ ዘሩን ተመልካች አይደለም። የአዲስ አበባ ኅብረተሰብ ዘር፣ ክልል፣ ቋንቋ አንድና አንድ ብቻ ናት፤ ኢትዮጵያ!

በመሆኑም አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች ከተሞች ያሉ ዘራቸው ኢትዮጵያ የሆነ በሚልዮን የሚቆጠሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሁሉም በዘሩ ሲቧደን ማን ሊያያቸው ነው? በሌሎች አካባቢ ያለውም እንደተጠበቀ በአዲስ አበባ ኅብረተሰብን የ27 ዓመት ኢሕአዴግ የዘርና/ቋንቋ ክፍፍል ውጤት ተጠቂ አድርጎታል።

ለማጠቃለልም ኢትዮጵያ ሀገራችን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታዋ መበታተን ይሆን ዘንድ ለ27 ዓመት የተዘረጋው የህወሓት/ኢሕአዴግ ዘረኛ ፖሊሲ ውጤቱ መክሸፍ መሆኑን ብንገነዘብም ንቀን የምንተወው ጉዳይ አይደለም። አሁንም ጥፋታችንንና ውድቀታችንን ብሎም እንደ ሀገር ከስያሜዋ ጀምሮ ኢትዮጵያን ለጠሉ፣ 27 ዓመት ሲገዙ አፋቸውን ሞልተው ሊጠሯት ለተቸገሩ "ተመስገን" እንበልና የተከበሩ ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ "ኢትዮጵያ…ኢትዮጵያ…አሁንም ኢትዮጵያችን…" ብለው ከፍ! አድርገዋታል። በዚች ኢትዮጵያ ጥሪ ውስጥ ሰንደቅ ዓላማችን እንደ መኸር ሰብል ተውለብልቧል፣ የሕዝባችን ደስታ ፈክቷል፣ ረሃቡ ሀገሩ የሆነችበት ወጣት ትውልድ ጨፍሯል፣ እናቶች አባቶች "ይሄን አሳየኸን፤ የመጨረሻውን ያሳምርልን" ብለዋል፣ ሕፃናት ቦርቀዋል፣ ምሁራን፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ድጋፍ ቸረዋል፣ ስደተኞች ሀገሬ ብለው ገብተዋል።

ይህ ሁሉ ሕዝባዊ ድጋፍና ደስታ ሊሠምር የሚችለው መሠረታዊ የሀገሪቷ ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት እንደተጠበቁ አሁንም ከሕዝብና ከሚመለከታቸው ጋር በምክክርና በመግባባት፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶቻችንን በመጠቀም የዘርና/ቋንቋን ግንብ ንደን የሁሉም ጎሳ/ነገዶች ክልል የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ስናደርግ ነው። የዚህ ጊዜ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ክልሉ ዳር ድንበሩ" እንላለን።

የዚህ ጽሁፋችን መደምደሚያ ምስጋና ይግባውና የኪነት ባለሙያው ቴዲ አፍሮ ኢ…ት..ዮ..ጵ..ያ.. ዜማ አድርገናል

"ባልፍም ኖሬ፡ ስለናት ምድሬ

እቧናት ክብሬ፤ ኸረ እኔስ ሀገሬ

ስንት የሞቱልሽ ለክብርሽ ዘብ አድረው

አልፈው ሲነኩሽ ባህርሽን ተሻግረው

የጀግኖች ሀገር ያዳም እግር አሻራ

ፈለገ ግዮን ያንቺ ስም ሲጠራ

እንኳን ሰማይ ላይ ባንዲራሽን አይቶ

ስምሽ ሲጠራ ማን ዝም ይላል ሰምቶ

ኢትዮጵያ ሲባል ማን ዝም ይላል ሰምቶ

ኢትዮጵያ…ኢትዮጵያ…ሀገሬ…ኢትዮጵያ. . .ሀገሬ. . .

ባንቺ አይደልወይ ወይ ክብሬ . . ."

በሚል ደጋግሞ ኢትዮጵያን. . .ሀገርን ከፍ ያደረገበት ሕዝባዊ አስተዋጽዎ ኢትዮጵያና ልጆቿ ትላንትም፣ ዛሬም፣ ነገም ለዘላለም አልፋና ኦሜጋ "**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!**" መሆናችንን በየመድረኩ፣ በየአካባቢው፣ በየቤቱ በአገኘው ምላሽ አስመስክሯል። እና አሁንም ኢ…ት..ዮ..ጵ..ያ.. ደግመን ደጋግመን ለዘላለም እንላለን።

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**

**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**
**ህዳር 7 ቀን 2011 ዓ.ም. (November 16, 2018)**

<u>**ማሳሰቢያ ፡**</u>

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ስልክ፡ 703 300 4302 , 6153064164

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin